# መጋረጃው ያልተነሳ ተውኔት፣ ያልተፈታ እንቆቅልሽ!

ከበልጅግ ዓሊ

የኔ copy right@

ተሰጥኦ ደርሷቸው፣ ዜማ የደረሱ፣
ዜማ ቢሰረቁ፣ ለዳኛ ከሰሱ።
እኔስ በተራዬ፣ የት ሂጄ ልክሰሰው
ዝምታዬን ሰርቆ፣ ዝም የሚለውን ሰው።

በእውቀቱ ስዩም

ወቅቱ በ1970 ዓ.ም. ነበር። ከፍተኛ 3፣ ቀበሌ 53፣ ሰንጋተራ አካባቢ በመንገድ ላይ ስጓዝ በማዴቦ እስኳድነት የተመደቡ የደርግ ገዳዮች በመንገድ ሲሄድ የነበረን ወጣት በአውቶማቲክ መሣሪያ ከጀርባው በጥይት በሳስተው ገደሉት። ወጣቱ በደረቱ ተደፋ። ነጻ እርምጃ ተካሂደበት ። የማዴቦ እስኳዶች እየተሳለቁ በላንድሮቨራቸው ከንፈው ሄዱ።

ይህንን ቀን ሳስታውሰው የዛ ወጣት ምስል ከፊቴ አይጠፋም። እናቱ ምን ሆነው ይሆን? አባቱስ? እህትና ወንድሞቹስ? ለእኔ በወቅቱ ከሌላ የማዴቦ እስኳድ ማምለጥ ስለነበረብኝ ጉዞዬን በጥድፊያ ቀጠልኩ። የዚህ ወጣት ምስል ለዘላለም አንግቤ ልዞር።

እኔም ብዙ አልቆየሁም። ታሰርኩ። ከሞቱት በላይ፣ ከቆሙት በታች እስከምሆን ተቀጠቀጥኩ። ቦታው ደርግ ጽሕፈት ቤት ውስጥ ነበር። የመንግሥቱ ኃይለማርያም ጽሕፈት ቤት። የብርሃኑ ከበደ የማሰቃያ ቢሮ . . .

በመገረፊያው ላይ ተሰቅዬ፣ አረመኔዎቹ እግሬን ሲተለትሉት፣ በዛ መንገድ ላይ በወደቀ ወጣት ቀናሁበት። ካለስቃይ በጥቂት ደቂቃዎች ሕይወቱ ባለፈችው። ሰው በሞት ይቀናል? እኔ ግን በሞት ቀናሁ። ሳያስበው፣ ሳይሰቃይ በተገደለው ወጣት ቀናሁ። ሕይወቱ በወጣትነቱ በተቀጨው ወጣት ቀናሁ። ምንኛ እረፍት ነው በዚች ፍትህ በተጓደለባት፣ ጀግና በተዋረደባት፣ አረመኔ በተከበረባት ሃገር ከመኖር መሞት ይሻላል ብዬ ቀናሁ።

ውስጥ እግሬ ላይ የሚደረገው ጌሾ ወቀጣ ሲጠነክር በሞተው እየቀናሁ፣ ሲረግብ በሕመሙ እየተሰቃየሁ ያንን የአረመኔዎች ተግባር ተቋቋምኩት። ዋ ! ሰው መሆን ! እስከ ዛሬ የዛ ወጣት ምስል ሰንጋተራ ላይ ተደፍቶ ይታየኛል።

ሁል ጊዜ ስለ ወጣትነቴ ሳስብ ይህ ወጣት ዓይኔ ላይ ይመጣል። በዛ ዘመን ብዙ መከራዎችን ያየሁ ቢሆንም የዛን ወጣት ምስል አንግቼ፣ ለተፈፀመበት ግፍ ፍትሕ ፍለጋ ለመታገል ለራሴ ቃል ገብቼ እኖራለሁ። ምን እሱ ብቻ እረ ስንቱ! . . .

አባትዋ ኮሎኔል ጣሰው ሞጆ ከ60ዎቹ ጋር በግፍ የተገደሉ፣ ልጃቸው ሳባ ጣሰው ከከፍተኛ 22፣ ቀበሌ 07 ተወስዳ፣ ቀበሌ 02 ጋ ከዛ ሁሉ ግፍ በኋላ በቀይ ሽብር

የተመታች ውብ ልጃገረድ የፍትህ ጥሪ አሁንም እንደ አዲስ ጆሮዬ ላይ ይጮኻል።

ልደታ ብሪሞ ገድል ውስጥ "ኢሕአፓ ይውደም!" አንልም ብለው በቆራጥነት የሞቱ የጆሆቫ ኃይማኖት ተከታዮች የፍትሕ ጥያቄ ጥሪ አሁንም ይሰማኛል።

ደርግ ጽሕፈት ቤት ውስጥ በብልትዋ ብረት ከተው ያሰቃይዋት፣ በሲጃራ ብልቷን የለበለቧት ጠይም ቆንጆ የስቃይ ጩኸት አሁንም አልቆመም። "ምነዋ ! አምላክ የሰጠኝን የሴትነቴን ምልክት! እንደማሰቃያ የተጠቀሙበት ይረሳል ወይ?!" ብላ ከመቃብረ ውስጥ ትጮኻለች።

መንግሥቴን ልትገለብጡ ነው በማለት በተለያ ጊዜ የተረሸኑ የጀግኖች ድምጽ ከፍ ብሎ ይጮኻል።

በልዩ ልዩ ምክንያት በደርግ ዘመን የተገደሉ ንፁሃን ዜጎች የፍትህ ጥያቄ በየቦታው ይሰማል። "እውነት የእኛ ሕይወት ፣ የእኛ የፍትሕ ጥያቄ፣ ከአንድ አሳታሚ ትርፍ ያነሰ ነው?" ብለው ይጠይቃሉ። "እውን እኛ በወጣትነታችን ለሃገራችን ስንል ባንሞት ኖሮ ዶክተር፣ ፕሮፌሰር መሆን አንችልም ነበር? አሳታሚ መሆን አንችልም ነበር?" ብለው ይጠይቃሉ።

ጦሪ ያጣች በረሃብ የምትሰቃይ፣ ልጅዋ በቀይ ሽብር የተገደለባት መንግሥቱ ልጆቼ ዶክትር ሆኑ ብሎ ሲፎክር ሰምታ "የእኔስ ልጅ ምን ይሆን ነበር?" ብላ ትጠይቃለች። ፍትህ፣ ፍትህ፣ እግዚዮ ፍትህ ትላለች። "መንግሥቱ በደጋፊዎቹ ልጆች የማሳተም መብቱ ሲጠይቅ፣ እኔ በጆንያ ነው ያረገዝኩት፣ የእኔስ የፍትሕ ጥያቄስ?" ብላ ትጮኻለች።

የዚህ ሁሉ የፍትሕ ጥያቄ ጩኸት ሌሎች የዓለም የግፍ ታሪኮች እንዳስታውስ አደረገኝ።

በአንድ ወቅት ለሥራ ፖላንድ ሃገር በነበርኩበት ወቅት ይሁዳውያን የተፈጁበት ቦታ ሄጄ ነበር። የተገረፉበት፣ በመርዝ ጪስ የታፈኑበት፣ የተገደሉበት፣ የተቃጠሉበትን ቦታ ተመለከትኩ። በዛ የብዙ ንፁሃን ደም በፈሰሰበት ቦታ ከዚህ እሰር ቤት የተረፉ አንዲት አሮጊት ይሁዳዊ ማብራሪያ ሲሰጡ አግኝቼ አንድ ጥያቄ ጠየቅኳቸው።

"ለመሆኑ ይህ በእርስዎ ላይ የተሰራው ግፍ ይረሳል ?" አልኳቸው።

በውስጡ ሃዘን በሞላው ደስ በሚል ፈገግታና ቀና ብለው ተመለከተውኝ። "በዚህ ቦታ የደረሰብንን ግፍ በፍጹም መርሳት አንችልም። ከዚህ የሥቃይ ጉድ የተረፍነውን ሰቆቃው ለዘላለም ሲከታተለን ይኖራል" አሉኝ በመቀጠልም፡ -

"እኛ አሁንም ከሞቱት በላይ፣ ከቆሙት በታች ነን። ሕይወታችን በአየነው ግፍ ተጨማልቃለች። እኛ ለመርሳት ስንታገል ኀሊናችን ደግሞ የፍትህ ጥያቄን እያነሳ እየታገለን ለዘላለም እንደተሰቃየን እንኖራለን። ዋናው ለምስክርነት አምላክ ያስቀመጠን ስለሆነ ስለ ግፉ እየተናገርን ዳግም እንዳይደገም መታገል ነው ከእኛ የሚጠበቀው።" አሉኝ።

ለአሮጊቷ በእኔ የደረሰውን ነገርኳቸው። እንባዬን ለማቆም ስታገል ሲመለከቱ ፡ -

“አልቅስ፣ አታቁመው! ቀጥል አልቅስ! ትንሽ ቀለል ሊልህ ይችላል። ግን በማልቀስ ብቻ በውስጥህ በማይጠፋ ቀለም ተጽፎ የሚገኘው የግፍ ማዕበል ይወጣል ብለህ አታስብ። እንደ እኔ ብታረጅ እንኳን፣ የግፉ ጊዜ ካለፈ ቢቆይ የእነዛ በግፍ ሲገደሉ ያየሃቸው ጓደኞችን የፍትሕ ጥሪ ለአይምሮህ እረፍት አይሰጥህም። ምን አደርክ ስለኔ?! ብለው ይጮኻሉ። ለዚህ ነው እኛ እስከ አሁን የሂትለርን ነፍስ ገዳዮች የምንከታተለው። መጠንከር ያስፈልጋል። ጊዜው አልፏል ብለው የሚጮኹ አይታጡም። ግፉ ለእነርሱ እንጂ ለእኛ አላለፈም። ሲገደል ያየኸው ወጣት ምስል ከዓይንህ የሚጠፋው ለፍትሕ በምታደርገው ጥረት እንጂ ለመርሳት በምታደርገው ሙከራ አይደለም።“ አሉኝ ።

“እኛ ግን እንደ እናንተ አቅም የለንም። ድህነት አለብን ። የግድያው ዋና መሪ መንግሥቱ ኃይለማርያም ዚምባዌ ውስጥ በድሎት ይኖራል። የእሱ ደጋፊዎች በዓለም ተበትነው ከሃገሪቱ በሰረቁት ገንዘብ በድሎት እየኖሩ ነው። የምዕራብ ሃገሮችም በሙጋቤ ላይ ተጽእኖ አያደርጉም።" አልኳቸው።

“ አዬ ! . . . የእኛ ከእናንተ የተለየ ይመስልሃል። አይደለም። ከጦርነቱ በኋላ ብዙዎቹ ወንጀለኞች በዓለም ተበትነዋል። ብዙዎችን ለፍርድ ብናቀርባቸውም እስከ ዛሬም ለፍርድ ያልቀረቡ ብዙ ናቸው። ግን እኛ ያላሰለሰ ጥረት እናደርጋለን። በተለይ ገንዘብ ካላቸው ቀላል አይደለም። ሚዲያውን ይገዛሉ። ራሳቸውን እንደ ጥሩ ዜጋ እንዲተረክላቸው በገንዘባቸው ቅጥረኞችን ይገዛሉ። ስንት የሚያናድድና ተስፋ የሚያስቆርጥ ጉዳይ አለ መሰለህ። በተለይ ከሁሉ የሚያሳዝነው የናዚን ግፍ የሚክዱ ስታገኝ ነው። ናዚ ይሁዳውያን ያጠፋው “በንግድ ሰለተሰማሩ ነው! ተንኮል ስለሚፈጽሙ ነው !” ሌላም ሌላም ምክንያት ይሰጣሉ። ሁሉም የተለያየ ምክንያት ይስጡ እንጂ ሂትለር ትክክል ነው ለማለት ነው። ወንጀላቸውን ለማድበስበስ ነው ጥረታቸው። በታሪክ ተወቃሽነትን ለመካድ ነው። ምን ምክንያት ቢያቀርቡ፣ ምን አድልዎ የተሞላበት ታሪክ ቢጽፉ ግፉ ግፍ ነው።”

በዚህ ሳምንት ሰንጋተራ ላይ በደረቱ ተደፍቶ በደሙ የተነከረው ወጣት፣ ሳባም፣ ጆሆባዎችም ሌሎችም በአረመኔዎች ግፍ የተንገላቱ ብዙዎች እንቅልፍ ነሱኝ። ለፍትህ የሚጮኹላቸው አጥተው፣ የስቃያቸው ዋና ምልክት የሆነው መንግሥቱ ኃይለማርያም መብቱ ተጣሰ ተብሎ በሃገሪቱ ታዋቂ ነን የሚሉ ምሁራን ስለመብቱ ሲከራከሩለት ስመለከት እንቅልፍ ነሳኝ። የተገደለ ልጅዋ አስከሬን ላይ መፈክር እንድታሰማ የተገደደች የእናትነት የመከራ ጩኸት እንቅልፍ ነሳኝ። ልጅህን አምጣ ተብሎ በእስተርጅና የተቀጠቀጠ አባት በሽምግልና የተሰበረ አጥንት የስቃይ ጩኸት እንቅልፍ ነሳኝ።

በዚህ ሳምንት የፍትሕ አድሎ ምንኛ በንዋይ ሊለወጥ እንደሚችል ተመለከትኩ። መንግሥቱ ለፍትህ ይቅረብ ማለት የሚከብዳቸው ፍጥረቶችን ተመለከትኩ። በድሆች የፍትሕ ጥያቄ ላይ የሚያላግጡ ምሁራንን ታዘብኩ።

ለመሆኑ ጎንደር ውስጥ ምሬቷን፡

መላኩ ተፈራ፣ የእግዜር ታናሽ ወንድም፣
የዛሬን ተውልኝ፣ ሁለተኛ አልወልድም ።

ብላ ላለቀሰች፣ ላስለቀሰች ደሃ እናት ማነው ፍትህ የሚጠይቅላት?

የእናትነት ማሕፀንሽ አላስችል ብሎሽ  ፍትህን ስትጠብቂ፣ የልጅሽ ገዳይ አለቃ መንግሥቱ በደጋፊዎቹ ሲሞገስ፣ በንዋይ በተገዙ አድርባዮች ፍትህ ሲጓደልብሽ ምን ታስቢ ይሆን? እውን አንቺም ኢትዮጵያዊ ነሽ ሊሉሽ ይሆን? እውን ስለ አንቺም ነው የምንታገለው ይሉሽ ይሆን? የሰሞኑ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ምሁሮች ምን ሊሉሽ ይሆን?

ለሃገር ሌላ አማራጭ አስባችኋል ተብለው በጥይት የተጨረሱት፣ ሬሳቸው በየመንገዱ የተጎተተው ጀግና ጄነራሎች ልጆቻቸው፣ ቤተሰቦቻቸው ይህንን የፍትህ አድሎ እንዴት ቻላችሁት? በዝምታ ልታልፉት?

የአባቶቻችን፣ የእናቶቻችን፣ የወንድሞቻችን፣ የእህቶቻችን የጓዶቻችሁ ደም ለፍትህ ይጮኻል! "አስቡኝ እኔ በወጣትነቴ ሕይወቴ ተቀጨ እንጂ እኔም ዶክተር፣ እኔም መጽሐፍ አሳተቃሚ፣ እኔም ፕሮፌሰር እሆን ነበር!" ብሎ ጥሪ ያቀርባል። እውን የአንድ የአሳታሚ ትርፍ ከእኔ የሕይወት ምንዛሪ በለጠ?" ብሎ ይጠይቃል። እፍረት ለዚህ አድሎዋዊ ፍትሕ!

ጎበዝ! ደበበ ሰይፉ ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ በሚልው ታላቅ ሥራው እንዲህ ይላል፡-

አወን ዛሬም በከተማችሁ፣ የሙታን ገኸ፣ ፋላጭ ቆራጭ አሳሪ፣
የሞተውን አሚች፣ የተቀበረውን ቀባሪ፣
የአስከሬናት ግብር አስገባሪ፣ የሙታን ላብ አቅራሪ፤
ስትልኩ ሳይ፣ የእብድ ሣቅ ያስቀኛል፡
መሠሪ ወጋችሁን ማወቄ ፣ ጠልቆ ይወጋኛል።
ግን ድሮም እንጂ፣ በአንበሳ መንጋጋችሁ፣ በነብር ማጉርጣችሁ፣
በጥንብ አንሳ መንቆራችሁ፣ በላሽ እባብ ምላሳችሁ፣
በጊንጥ በዘንዶ ጅራታችሁ፣ በገበሎ ትንፋሻችሁ፣ . . .
በሌላማ ማን ሊያውቃችሁ? ማን ሊያውቃችሁ ?

ከዚህ የበለጠ የዘመኑን ፍትሕ አጉዳዮችን የሚገልጽ ምን ግጥም ይኖራል? እረ በደርግ ዘመን ምን ያልተጎዳ አለ? የሃማኖት መሪዎች፣ የኃይለሥላሴ ዘመን ባለስልጣን ቤተሰቦች እንዴት ይህንን ግፍ በዝምታ ታልፉታላችሁ? ነገ በሕዝብ ፊት ልጁ የተገደለባት፣ የምትወደው ባሏ ከቤት ወጥቶ የቀረባት፣ ጧሪ ያጣ ሽማግሌ  "ምነው በድህነቴ ምክንያት ፍትሕ ነፈጋችሁኝ?" ቢሏችሁ ምንድነው መልሳችሁ? "ለመንግሥቱ መጽሐፍ የኮፒ ራይት ስታገል የእናንተን ፍትህ ረሳሁት!"

ለነገሩ ብዙዎቹ በዚህ የፍትሕ አድሎ የሚሳተፉ፣ በግፉ በቀጥታም ይሆን በተዘዋዋሪ የተሳተፉ ናቸው። ደበበ ሰይፉ በመቀጠል፡ -

ከቶ እዚህ፣ ማን ምን አለው፣ ከእናንተ ወሬ አሉባልታ፣
ከእናንተ ዝባዝንኬ፣ ከእናንተ ተረብ እሩምታ?
አወን፣ እንደተረታችሁ የደላው ሙቅ ያኝካል፣
ሕይወት በመታደግ ሳይሆን፣ በጥናቷ ብቻ ይረታል።
እና እዚያው እርስ በርሳችሁ ብትመሣጠሩ፣ ዕፁብ ድንቅ ተዓመር ብትለፍፉ፣
ተረት ተረታችሁን ብታወጉ፣ በእኔነት ማራቶን ብትዳፉ፣
በቋንቋ ስለት ብትዋጉ፣ ለክብር ለስም ብትዳሙ ብትጋፉ፣

በአለሁ ባይነት ብትፏድዱ፣ ብትጣፉ፣ . . .
በዚህ ሙት ሕዝብ፣ በድክመቱ በትልቁ፣
በፈተናው ብትበልጡ፣
በሱ ውድቀት እናንተ፣ እርካብ ብትረግጡ፣
በብሶቱ ብትፈይዱ፣
በመክሊቱ ብትነግዱ፣
ይህ ፍፁም ባድማ፣ ይህ ፍፁም ድቅድቅ ጨለማ፣
እሚበራ እንዳይመስላችሁ፣ በእናንተ የይስሙላ ቁራጭ ሻማ።

ግን መጋረጃው ያልተፈታ ተውኔት፣ ያልተፈታ እንቆቅልሽ፣ አለውና ጨለማ፣
ነፋስ - እሳተ ገሞራን፣ ሊታቀፍ ይቻላልና ጠፍ ባድማ፣

ዐይን ያለው ይይ!
ልብ ያለው ያስተውል!
ጆሮ ያለው ይስማ !

ይቀጥላል !

Beljig.ali@gmail.com

ለንደን፣ ጥር 2004 (ጃንዋሪ 2012)